# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## የአውሮፓ ክፍል
## Ethiopian People’s Revolutionary Party (EPRP)
## Europe Section

---

**<u>የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የአውሮፓ ክፍል 6ኛው የአባላት መደበኛ ስብሰባ የአቋም መግለጫ</u>**

ቀን፡- ነሐሴ 28፣ 1998 ዓ. ም.

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የአውሮፓው ክፍል 6ኛ የአባላት መደበኛ ስብሰባ ጀርመን፣ ፍራንክፈርት ከተማ ውስጥ ነሐሴ 25 እና 26 ቀን፣ 1998 ዓ. ም. ተካሄደ። ጉባኤው የኢትዮጵያን ወቅታዊ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ መርምሯል። በድርጅቱ የአለፉት 34 ዓመታት አኩሪ ታሪክ ውስጥ የሀገራችን አንድነት የሚጠበቅበት፣ የህዝቧ ሉዐላዊነትና ዴሞክራሲያዊ መብት የሚከበርበት መልካም አስተዳደርን ለማምጣት ሲታገሉ የወደቁ፣ መከራና ችግርን የተቀበሉ፣ አሁንም በመቀበል ላይ ያሉ ጀግና ጓዶቻችንን አስቧል። የትግል አደራቸውንም ልብ ብሏል። የትግል ቃል ኪዳኑን አድሷል። የሀገሪቱን፣ የአካባቢዋንና የዓለም አቀፉን ወቅታዊ ሁኔታም መርምሮና ተወያይቶ ተክክለኛ ግንዛቤ ወስዷል።

የአለንበት ወቅት ከግንቦት፣ 1997 ዓ. ም. ምርጫ ማግስት አንስቶ የሕወሓት/ኢህአዴግ አምባገነን አገዛዝ ከበፊቱም ያካሂድ የነበረውን ግድያ፣ እመቃና እስር አጠናክሮ እየቀጠለ ያለበት ሁኔታ ነው። ሕዝብ በምርጫ ድምፁን የሰጣቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች፣ የነፃው ጋዜጠኞች አባላት፣ የሙያ ማህበራትና የሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች፣ እንዲሁም ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሌሎችም ኢትዮጵያዊያን ወደ እስር ቤት ተወርውረዋል። የጠባብ ብሄርተኛውን ገዥ ቡድን አፈና እና ግድያ በመቋቋም መራራ መስዋዕትነትን እየከፈለ የህዝብ ልሣን የነበረው ነፃው ፕሬስ ደብዛው ጠፍቷል። በአረመኔው የመለስ ቡድን ታማኝ የውሸት ጋዜጦች ተተክቷል።

በዚህ መልክ አገዛዙ ያደረገውንና እያደረገ ያለውን ግድያና እስራት ለመቋቋም፣ ብሎም ለማክሸፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያካሄደውንና እያካሄደ ያለውን ትግል፣ የከፈለውንም መስዋዕትነት ጉባኤው በአክብሮት አስቦታል። ይህንንም ተከትሎ በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በሀገር ቤት በሚኖረው ወገኑ ላይ የሚደርሰው ግፍ አንገብግቦት በጋራ (በኅብረት) እየተሰባሰበ ያካሂድ የነበረው የተጠናከረ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የሚረሳ አይደለም። ዛሬም ሕዝባዊ ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል በሚገባው ወሳኝ ወቅት፣ ከተቃዋሚው ጎራ ተንሸራተው በሕዝብ ድምፅ ስርቆትና በንፁሃን ደም ተንክሮ የተፈጠረውን አሻንጉሊት የመለስ ፓርላማ የተቀላቀሉትንም አውግዟል። በታሪክ ተጠያቂ መሆናቸውንም ጉባኤው አስምሮበታል።

በቅርቡም ሁሉን አቀፍ ባልሆነ፣ የሀገርን አንድነትና ህልውና ጥያቄ ላይ በሚጥል መንገድ የተወሰኑ ቡድኖች የፈጠሩት ትብብርም በውጭ ይካሄድ በነበረው የተጠናከረ ትግል ላይ የበኩሉን ውሃ እንደቸለሰበት እውነት ነው። የውጭ ኃይላትም እየተካሄደ ላለው ሕዝባዊ ትግል ያሳዩት ድጋፍ ከልብ የመነጨ አልነበረም። አሁንም የነመለስን አገዛዝ እየደገፉና እያጠናከሩ መሆኑን እንገነዘባለን። ይህም ሕዝባችን መልካም አስተዳደርን ለማምጣት የሚያደርገውን ትግል እየጎዳው መሆኑን ጉባኤው ተገንዝቧል።

አሸባሪው አምባገነን የመለስ አገዛዝ ከሚያራምደው የዘር ፖለቲካ በተጨማሪ አንዳንዶች በስሜታዊነት፣ ሌሎች ደግሞ አፉኝና ከፋፋይ የሆነውን ብልሹ አስተዳደርና ፖሊሲ ለተወሰነ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝባችን በመስጠት የሚያራምዱት የጅምላ ውንጀላ ሀገርን ወደጥፋት፣ ሕዝብን ወደ ዕልቂት የሚገፋፉና የሚጋብዝ መሆኑን ጉባኤው አስታውሷል። ሁሉም ዓይነት ፅንፈኝነት ለሕዝባችንንና ለሀገራችን ጠንቅ በመሆናቸው መዋጋት እንደሚገባ ለወገን ጥሪውን አስተላልፏል። በሱማሌ እየተከሰተ ያለውን ሁኔታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በትኩረት ሊመለከተው የሚገባ ክስተት እንደሆነና በሞቃዲሾ እራሱን የሰየመው ቡድንም በኢትዮጵያ ግዛት ላይ የሚያነሳው የይገባኛል ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ጉባኤው አምኖበታል። በአንፃሩም ይኸው የነመለስ ቡድን የጥፋት አገዛዝ በሱማሌ ሕዝብ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ የሚያራምደው ፖሊሲ ከሀገራችን አልፎ ለአካባቢውም ጦስ ሊሆን የሚችል ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል ተገንዝቧል።

በአጠቃላይ የሀገራችንና የሕዝባችንን ህልውና የሚፈታተኑትን ችግሮች፣ ሁሉን አቀፍ በሆነ ሂደትና ጥረት እንጅ በተወሰኑ ወገኖች ብቻ የሚፈታ እንዳልሆነ ጉባኤው አፅንዖት ሰጥቶ ተነጋግሮበታል። ስለዚህም ተሳታፊው ድርጅታችን (ኢሕአፓ) አባል የሆነበት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ትግሉ በጋራ ተካሂዶ፣ ሕዝባችን ለጋራ ድል ይበቃ ዘንድ የአስቸኳይ ጊዜ ግብረ-ኃይል እንዲቋቋም፤ የፖለቲካና የሲቪክ ማህበራት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ሴቶችና ወጣቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች ወዘተ የሚሳተፉበት የጋራ ጉባኤ እንዲጠራ የአስተላለፈውን ውሳኔ እንደሚደግፍ፣ ለተግባራዊነቱም እንደሚታገል ጉባኤው ቃል ገብቷል። በአውሮፓ የሚገኙ ሌሎች ኢትዮጵያዊያን ድርጅቶችና ግለሰቦችም ለዚህ የጋራ ትግል ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ እንዲሰጡ ጥሪውን በማስተላለፍ ጉባኤው ተጠናቋል።

በሕወሓት/ኢህአዴግ የተሰረቀው የሕዝብ ድምፅ ይመለስ!
ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያቸንፋል!

Ethiopian People’s Revolutionary Party (EPRP), Europe Section
Postfach 103604, 50476 Koln, Germany